## ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 29 ኛ ሳምንት

## ትንሣኤ

**ዓላማ**

- ስለክርስቶስ ትንሣኤ መማር፡፡

**ምንባብ**

- ማቴ.28÷1-8 ማር.16÷1-8 ዮሐ. 21፣1-14

**መግቢያ**

- ጌታችን ከተነሣ በኋላ ለደቀመዛሙርቱና ለሌሎችም ምዕመናን በተለያዩ ጊዜያት ለ40 ቀናት ይገለጥላቸው ነበር፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ጌታችን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ የተገለጠበትን ታሪክ እንማራለን፡፡

**ትምህርቱ**

- ጌታችንን እየተከተሉ የሚያመስግኑትን ሕፃናትንና ሕዝቡ የተመለከቱት አይሁድ በጌታችን ላይ ቀኑበት፡፡ሊገድሉትም ወሰኑ፣የሐሰት ምሥክር አቁመው፣ከሠሱት፣
- አርብ እለትም ተሰቀለ፣ ሞተም፡፡ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የተባሉት ሁለት ሰዎችም ከመስቀል አውርደው፣ ቀበሩት፡፡ኒቆዲሞስን ታስታውሳላችሁ?..... ከመምህር ጋር ተወያዩ
- በሦስተኛውም ቀን መግደላዊት ማርያም ከሌሎች ቅዱሳት እንስት ጋር ሥጋውን ሽቱ ሊቀቡት ወደ ጌታችን የመቃብር ሥፍራ መጡ፡፡ ***ማን ድንጋዩን ያንከባልልናልም*** ይባባሉ ነበር፡፡
- ሲደርሱ ግን መልአኩ ድንጋዩን አንከባሎ ነጭ ልብስ ለብሶም ተቀምጦ ተመለከቱ፡፡ እጅግም ፈሩ መልአኩም ***"እናንተስ አትፍሩ የናዝሬትን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና ተነሥቷ ከዚህ የለም የመቃብሩንም ሥፍራ ተመልከቱ"***
- ሴቶችም ወደ መቃብሩ ሥፍራ ተመለከቱ መልአኩ እንደነገራቸውም ጌታችን በዚያ አልነበረም፡፡ይህን በመስማታቸው እጅግ ተደስተው ሄዱ፡፡መልካሙን የትንሣኤ ዜናም ለደቀመዛሙርቱ አበሰሩ፡፡
- መግደላዊት ማርያምና ሌሎቹ ሴቶች የጌታን መነሣት ለደቀመዛሙርቱ አበሠሩ፣ ከጥቂት ቀናት በኋላም ደቀመዛሙርቱ በማታ ዓሣ ሊያጠምዱ ወጡ፡፡ሌሊቱን ሙሉ ምንም አላገኙም፡፡
- በጠዋትም ክርስቶስ በሚያጠምዱበት ዳርቻ ቆሞ ተገለጠላቸው፡፡እርሱ መሆኑን ግን አላወቁም፡፡ጌታችንም ***"ልጆች ሆይ አንዳች የሚበላ አላችሁን?"***
- ***"የለንም"*** ብለው መለሱለት፡፡እርሱም ***"መረቡን በታንኳይቱ በስተቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ"*** አላቸው፡፡
- ሙሉ ሌሊቱን ሞክረው ባያገኙም፣መረባቸውን እንደታዘዙት ጣሉ፡፡ብዙ ዓሣ አጠመዱ ለመጎተት እስኪያቅታቸውም ተጨንቁ፣መረቡ ሳይቀደድም ጎትተው አወጡት ፍምና ዓሣም ሞልቶበት ነበር፡፡
- ዮሐንስም ጌታ መሆኑን አውቆ ለጴጥሮስ ነገረው፡፡ጴጥሮስ ልብሱን አውልቆ ከባሕሩ መሐል ነበርና ደንግጦ ልብሱን ይዞም ወደ ባሕር ገብቶ ወደ ጌታ መጣ ተባብረውም መረቡን ካወጡ በኋላ፡፡ጌታችን ***"ኑ ብሉ"*** አላቸው፡፡
- ሊጠይቀው የደፈረም አልነበረም፡፡ጌታ መሆኑን አውቀው ነበርና፡፡ባርኮም ሊበሉ ሠጣቸው፣ በሉም፡፡ ይሄን ከተነሣ በኋላ ሊገለጥላቸው ሦስተኛው ጊዜ ነበር፡፡

**መዝሙር**

አማን በአማን (4)
ተንሥአ እምነ (4)

ይቆየን፡፡